# የCAMBRIDGE ከተማ አስተዳደር

የምርጫ ኮሚሽነሮች ቦርድ

689 Massachusetts Ave Ste 1, Cambridge, Massachusetts 02139-3302 ▪ ስልክ ቁጥር 617-349-4361 ▪ TTY፡- 617-492-0235
ፋክስ፡- 617-349-4366 ▪ ኢሜይል፡- Elections2@cambridgema.gov ▪ ድር-ጣቢያ፡- www.cambridgema.gov/election

ኮሚሽነሮች
Ethridge A. King, Jr.
Larry W. Ward
Charles J. Marquardt
Thomas J. Stohlman, Jr.

ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር
Tanya L. Ford

ረዳት ዳይሬክተር
Lesley A. Waxman


**ውድ የCambridge መራጭ፣**

**የምርጫ ኮሚሽነሮች ቦርድ እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም ሕጎች ምዕራፍ 630 ሥር <u>እ.ኤ.አ የኖቬምበር 4 ቀን 2025 ዓ.ም የማዘጋጃ ቤት ምርጫ</u> የድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የሚቀርበውን የድምጽ መስጫ ወረቀት ጥያቄ #1 ጽሑፍ እንዲሁም የውሳኔ ሀሳቡን ማጠቃለያ እና እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም ሕጎች ምዕራፍ 630 መሠረት ደጋፊ እና ተቃዋሚ መከራከሪያዎቹን ለCambridge መራጮች ያቀርባል።**

City Council (የከተማ ምክር ቤት) አዲስ የከተማ አስተዳደር ቻርተር እንዲጸድቅ የውሳኔ ሀሳብ ያቀረበ ሲሆን፣ ይህ ቻርተር የCambridgeን የመንግሥት አወቃቀር የሚወስነው ሕግ ነው። ቻርተሩ የCity Council፣ የCity Manager እና የትምህርት ቤት ኮሚቴ ሥልጣኖችን ይደነግጋል።

City Council በውሳኔ ሀሳብ የቀረበው አዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር ተቀባይነት እንዲያገኝ እ.ኤ.አ ኖቬምበር 4 ቀን 2025 ዓ.ም ላይ በሚካሄደው ቀጣዩ ሁለት ዓመታዊ ምርጫ ለCambridge ከተማ አስተዳደር መራጮች በሚከተለው ጥያቄ መልክ እንዲቀርብ እ.ኤ.አ ኤፕሪል 14 ቀን 2025 ዓ.ም ላይ ድምጽ ሰጥጦ ወስኗል፡-

| | |
|---|---|
| **ጥያቄ 1** | ለCambridge ከተማ አስተዳደር ቻረተር የሚያቋቁም ሕግ ይጽደቅ? |

**የውሳኔ ሀሳብ ማጠቃለያ፡-** City Council በውሳኔ ሀሳብ ያቀረበው ለውጥ የከተማ አስተዳደሩ በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ የሚያደርገው በአጠቃላይ ሕጎች ምዕራፍ 43፣ ክፍል 93 ሥር የተደነገገውን Plan E ቻርተር በአዲስ የከተማ አስተዳደር ቻርተር ይተካል።

በአዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር ሥር Cambridge የCity Council/City Manager ቅርጽ ባለው መንግሥት መተዳደሩን ይቀጥላል። በተመጣጣኝ ውክልና ሁለት ዓመት ለሚዘልቅ የሥልጣን ዘመን እንዲያገለግሉ በሰፊው የማዘጋጃ ቤት መራጭ የታጩ እና የተመረጡ ዘጠኝ አባላት ያሉት City Council በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሕግ አውጪ ሥልጣን ይኖረዋል። በእያንዳንዱ የሥልጣን ዘመን ላይ ተመራጭ የCity Council አባላት 2 ዓመት ለሚዘልቀው የሥልጣን ዘመናቸው እንደ ከንቲባ እና ምክትል ከንቲባ የሚያገለግሉትን ግለሰቦች ከመካከላቸው በአብላጫ ድምጽ ይመርጣሉ። በአሁኑ Plan E ቻርተር ላይ እንዳለው አሠራር ከንቲባው ለሁሉም ሥነ-ሥርዓታዊ ጉዳዮች እንደ የከተማ አስተዳደሩ ኃላፊ እውቅና ይሰጣቸዋል፣ የCity Council ስብሰባ መሪ ይሆናሉ፣ የትምህርት ቤት ኮሚቴ አባል ይሆናሉ፣ ድምጽ በድምጽ የመሻር ሥልጣን አይኖራቸውም እንዲሁም ሌላ ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ካለው ሥልጣን ጋር ተመሳሳይ ሥልጣን ይኖራቸዋል። City Council የCity Manager፣ የCity Auditor እና የCity Clerk ባለሥልጣናትን በቀጥታ እየሾመ ይቀጥላል።

በአዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር መሠረት City Council የከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የሚያገለግሉ እና በCity Manager ኃላፊነቶች ውስጥ ወይም በቻርተሩ ሥር የተመደቡላቸው የከተማ አስተዳደር ጉዳዮችን በሙሉ በአግባቡ በማስተዳደር ረገድ ለCity Council ተጠያቂ የሚሆኑ City Manager መሾሙን ይቀጥላል። City Manager

የCity Council በሚሰጣቸው ድምጾች እና ውሳኔዎች መሠረት እና በመተዳደሪያ ደንቦች፣ የገንዘብ ድልደላ ትዕዛዞች እና የብድር ፈቃዶች ላይ እንደሚገለጸው በCity Council የጸደቁ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

በአዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር መሠረት፣ የCambridge የትምህርት ቤት ኮሚቴ ሁለት ዓመት ለሚዘልቅ የሥልጣን ዘመን በሰፊው የከተማ አስተዳደሩ የማዘጋጃ ቤት መራጭ በታጩ እና በተመረጡ ስድስት አባላት እና እንደ ሰባተኛ አባል በሚያገለግለው ከንቲባ እየተዋቀረ ይቀጥላል። በአዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር መሠረት፣ የትምህርት ቤት ኮሚቴ አባላት ከተመረጡ አባላቶቻቸው መካከል እንደ ሊቀመንበር የሚያገለግሉ አንድ ግለሰብ እና እንደ ምክትል ሊቀመንበር የሚያገለግሉ ሌላ ግለሰብ ይመርጣሉ። የትምህርት ቤት ኮሚቴው የትምህርት ቤት ሥርዓቱን የማስተዳደር ኃላፊነት የሚሰጠው የትምህርት ቤት ዳይሬክተር መምረጥ እና ማስወገድ፣ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሥርዓቱን ለማስተዳደር ምክንያታዊ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች እና ቁጥጥሮችን መንደፍ እንዲሁም በCity Council ውሳኔ የሚደለደለው የትምህርት ቤት መምሪያው ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በጀት አስተዳደርን ማጽደቅ እና በበላይነት መቆጣጠርን ጨምሮ በMassachusetts አጠቃላይ ሕጎች፣ ቻርተር እና መተዳደሪያ ደንቦች መሠረት ለትምህርት ቤት ኮሚቴዎች የተሰጡ ሥልጣኖችን በሙሉ እንደያዘ ይቀጥላል።

አዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር ለመረዳት ቀላል እና ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን በአንቀጾች የተደራጀ እና ከፆታ ገለልተኛ ቋንቋን የሚጠቀም ነው።

አዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር አዲስ የቁጥጥር እና የፋይናንስ አሠራሮችን ያቋቁማል።

አዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር የከተማ አስተዳደሩን በደረጃ አሰጣጥ ምርጫ ተመጣጣኝ ውክልና የሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በሕግ ያስቀምጥ እና የከተማ አስተዳደሩ የምርጫ ኮሚሽነሮች ቦርድ ደንቦችን ይፋ እንዲያደርጉ እና የከተማ አስተዳደሩ የማዘጋጃ ቤት ምርጫዎች ታማኝ እና እንከን የለሽ ሆነው መከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነ የደረጃ አሰጣጥ ምርጫ ድምጽ መስጫ ወረቀት እና የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ ላይ ለውጦች እንዲያደርጉ ያስችላል።

አዲሱ የከተማ አስተዳደር ቻርተር የሕዝብ ተሳትፎን የሚያበረታታ ሲሆን፣ በተነሳሽነቶች እና በሕዝበ ውሳኔ በኩል የሚቀርቡ የሕዝብ አቤቱታ እርምጃዎችን የሚፈቅድ ሕግ ያስቀምጣል።

**እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም ሕጎች ምዕራፍ 630 መሠረት፣ የምርጫ ኮሚሽኑ ለCambridge መራጮች ብቻ ለቀረበ ጥያቄ ደጋፊ እና ተቃዋሚ መከራከሪያዎችን ማተም ይጠበቅበታል። እነዚህ መከራከሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፦**

| **በውሳኔ ሀሳብ የቀረበውን ቻርተር የሚደግፍ መከራከሪያ** |
|---|

ቻርተር ሲባል የአካባቢ መስተዳድሩን መዋቅር እና አደረጃጀት የሚወስነው ለከተማ አስተዳደሩ እጅግ ወሳኝ የሆነ ሕጋዊ ሰነድ ነው። የCambridge ከተማ አስተዳደር ከ85 ዓመታት በፊት እ.ኤ.አ በ1940 ዓ.ም የPlan E ቅርጽ ያለው መንግሥት ከጸደቀ በኋላ ቻርተሩን ገምግሞ አያውቅም። በከተማዋ እና በዓለም ላይ ከፍተኛ ለውጥ የታየ ቢሆንም፣ ቻርተራችን ሳይቀየር ባለበት ቆይቷል።

የድምጽ መስጫ ወረቀት ጥያቄው ላይ አዎ የሚል መልስ ከተሰጠ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በከተማ አስተዳደሩ Charter Review Committee (የቻርተር ግምገማ ኮሚቴ) እና City Council መካከል በተደረጉ ውይይቶች የተዘጋጀው አዲስ ቻርተር እንዲጸድቅ ያደርጋል። አዲሱ ቻርተር በተሻለ አደረጃጀት፣ ፆታ ገለልተኛ ቋንቋ እና ለመረዳት ቀላል እና ለሕዝብ ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን በማለም በቀረቡ አዲስ ትርጓሜዎች አማካኝነት ቋንቋውን ይበልጥ ግልጽ እና ዘመናዊ ያደርጋል። አዲሱ ቻርተር የከተማ አስተዳደሩን City Council/City Manager ቅርፅ የያዘ የመንግሥት መዋቅር ያስቀጥል እና አዲስ የቁጥጥር እና የተጠያቂነት አሠራሮችን በሕግ ያስቀምጣል። አዲሱ ቻርተር የከተማ አስተዳደሩን የትምህርት ቤት ኮሚቴ

እንዳለ የሚያስቀጥል ቢሆንም፣ አሁን ግን ሊቀመንበሩ ከአባላቶቹ ዘንድ እንዲመረጥ ይጠይቃል። አዲሱ ቻርተር የተሻለ የበጀት ዕቅድ አወጣጥ እና ግልጽነትን የሚያበረታቱ አዲስ የበጀት ሂደቶች እና ፖሊሲዎችን በሕግ ያስቀምጣል። አዲሱ ቻርተር የከተማ አስተዳደሩን በደረጃ አሰጣጥ ምርጫ ተመጣጣኝ ውክልና የሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በሕግ ያስቀምጥ እና በተመሳሳይ ሰዓት ለዘመናዊ የቆጠራ ዘዴዎች፣ የትርፍ ድምጽ ዝውውሮች እና ሌሎች ሂደቶች አዲስ ደንቦች ተፈጻሚ የማድረግ ችሎታን ይሰጣል።
አዲሱ ቻርተር የCambridgeን መንግሥት ዘመናዊ እያደረገ በተመሳሳይ ሰዓት ለከተማ አስተዳደሩ መራሽ የሆኑት የእኩልነት፣ የፍትሕ፣ የብዝሐነት፣ የማኅበረሰብ ተሳትፎ እና የአካታችነት እሴቶች ያለንን ቁርጠኝነት ያጠናክራል። አዎ የሚል ድምጽ የከተማ አስተዳደሩ መንግሥታዊ መዋቅር እና እሴቶች ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ጸንተው መቀጠላቸውን ያረጋግጣል።

## በውሳኔ ሀሳብ የቀረበውን ቻርተር የሚቃወም መከራከሪያ

የCambridge ቻርተር እ.ኤ.አ በ1940 ዓ.ም ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በስቴት ሕግ መሠረት የከተማ አስተዳደሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የሚያገለግሉ City Manager በCity Council የሚሾሙበት "Plan E" የተሰኘ የመንግሥት መዋቅር ሥር ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። የእኛ Plan E ቻርተር ውጤታማ፣ ሙያዊ እና ምላሽ ሰጪ መስተዳድርን በማስቻል ለከተማ አስተዳደሩ በጥሩ ሁኔታ ያገለገለ ሲሆን፣ የብዝሐ ነዋሪዎቻችንን ፍላጎቶች እንድናሟላ እና በCommonwealth ውስጥ እጅግ ከበለጸጉ ከተሞች መካከል አንዷ እንድንሆን ሲረዳ ቆይቷል። ይህ ስኬት እንዳለ ሆኖ፣ አንዳንድ ተሟጋቾች ግን በዚህ የድምጽ መስጫ ወረቀት ጥያቄ በኩል የከተማ አስተዳደሩ አሁን ያለውን የPlan E ቻርተር እንዲተው እና አዲስ ቻርተር እንዲያጸድቅ ይፈልጋሉ። የከተማ አስተዳደሩ በPlan E የያዘው የCity Council/City Manager የመንግሥት መዋቅር፣ የትምህርት ቤት ኮሚቴ እና የተመጣጣኝ ውክልና ምርጫዎች ሂደት ቀጣይነት ስለሚኖራቸው አዲስ ቻርተር ማጽደቅ አስፈላጊ አይደለም። እንደ የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ እና በጀት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ክፍሎቹ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ በውሳኔ ሀሰቡ የቀረቡ ለውጦች የከተማ አስተዳደሩ ቀድሞውኑ በመተዳደሪያ ደንቦች ወይም በፖሊሲ በኩል የሚከተላቸው እንደመሆኑ መጠን እነዚህም አላስፈላጊ ናቸው። በተመሳሳይ የከተማ አስተዳደሩ የምርጫ ሂደቶች ላይ ለውጦች ለማድረግ አዲስ ቻርተር ማጽደቅ አያስፈልግም። በስተመጨረሻም በውሳኔ ሀሳብ የቀረቡት አንዳንድ ለውጦች በሕግ አውጪ እና ሕግ አስፈጻሚ ቅርንጫፎች መካከል ያሉትን ከለላዎች በማፍረስ የሥልጣን ክፍፍልን የሚሸረሽሩ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን የሚጎዱ ናቸው።

በውሳኔ ሀሳብ የቀረበው ቻርተር አላስፈላጊ እና የPlan E ቻርተር ቀድሞውኑ ከሚያስገኛቸው የሚከተሉት ስኬቶች ባሻገር ምንም የተለየ ነገር የማይፈጥር ነው፡- መልካም አስተዳደርን ማበረታታት እና የከተማ አስተዳደሩ ለእኩልነት፣ ብዝሐነት፣ የማኅበረሰብ ተሳትፎ እና አካታችነት ያለውን ቁርጠኝነት ወደፊት ማራመድ። የከተማ አስተዳደሩ አሁን የሚተገብረው Plan E ቻርተር በአግባቡ የሚሠራ ሲሆን፣ አይ የሚል ድምጽ ይህ ቻርተር በ21ኛው ክፍለ ዘመን የከተማዋን ነዋሪዎች በውጤታማነት እያገለገለ መቀጠሉን ያረጋግጣል።

**የድምጽ መስጫ ጥያቄ ማጠቃለያ እና የቀረበውን አዲስ የከተማ ቻርተር ሙሉ ለሙሉ ለማየት፣ እባክዎን [www.cambridgema.gov/charterquestion](www.cambridgema.gov/charterquestion) ን ይጎብኙ።**